Montgomery County Public Schools
UNLEASHING POTENTIAL



Summer RISE
Connecting Students to Careers

# ሠመር ራይዝ 2026 የወላጅ/የሞግዚት ስምምነት
# Summer RISE 2026 Parent/Guardian Agreement

Department of College & Career Readiness
MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS
850 Hungerford Drive, Room 257, Rockville, Maryland 20850

## የወላጅ/የሞግዚት/የብቁ ተማሪ ስምምነት ሠነድ፡- PARENT/GUARDIAN/ELIGIBLE STUDENT CONSENT

ይህ የሠመር ራይዝ ፕሮግራም የተነደፈው በአሁኑ ወቅት በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት በመከታተል ላይ ለሚገኙ 11ኛ ክፍል ለገቡ እና 12ኛ ክፍል ለሚገኙ ተማሪዎች በሠመር ወቅት የሙያ ሥራ ልምዶችን ለመቃኘት እንዲያስችላቸው ነው።

1. እርስዎ፣ ወላጅ/አሳዳጊ እንደመሆንዎ፣ 2026-2027 የትምህርት አመት MCPS 11ኛ ክፍል ወይም 12ኛ ክፍል የሚመዘገብ/የምትመዘገብ ተማሪዎ እንደሚሳተፍ/እንደምትሳተፍ በመረዳት ተስማምተዋል..
2. ከጁን 22, 2026 ጀምሮ እስከ ጁላይ 24, 2026 የሚካሄደው የሠመር ራይዝ መርሃ ግብር እስከ 5 ሳምንታት ድረስ እንደሚካሄድ እና በተመደበ(ች)በት የንግድ መደብር፣ ድርጅት፣ ኤጀንሲ፣ ወይም ተቋም ("የሙያ ልምድ ለመስጠት ተቀባይ ድርጅት") ባለበት በአካል በመገኘት ወይም ቨርቹዋል በሙያ ላይ የተመሰረተ የትምህርት ልምድ ቢያንስ 50 ሰአታት በእጅ እየተሠራ እውቀት ማግኘት እና ልምድ መቅሰም እንደሚያስፈልግ በመረዳት ስምምነት ተደርጓል") ተማሪው(ዋ) በቀን ከ 8 ሰአት ያልበለጠ እና በሳምንት ከ 40 ሰአት የማይበልጥ በስራ ልምምድ አስተናጋጅ ቦታ ላይ ያሳልፋል/ታሳልፋለች። የሠመር ራይዝ ተሣታፊዎች ከሰኞ እስከ ዓርብ ከ 7:00 AM በፊት አይጀምሩም ወይም ከ 6:00 P.M. በፊት ያጠናቅቃሉ። ተማሪዎች የገንዘብ ድጎማ ክፍያ ለማግኘት በፕሮፌሽናል ክህሎት እና በፋይናንሻል ትምህርት አውደ ጥናት ላይ መሳተፍ እና 50 ሰአቱን ማጠናቀቅ ይጠበቅባቸዋል። ከሙያ ልምድ ሰጪ ተቋም የሚመለከተው የሥራ ባልደረባ ("Career Experience Host Designee(s)") የሠመር ራይዝ ፕሮግራም " Summer RISE Program" ሲጠናቀቅ ተቀባይነት ያለው 50-ሠዓት የሙያ ልምምድ ማረጋገጫ ይሰጣል።
3. የተደረገ ስምምነት፡- ተማሪው(ዋ) በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ሠመር ራይዝ ኢንተርንሽፕ ፕሮግራም ላይ ለማገልገል ከመረጠ(ች) እና እንዲሳተፍ/እንድትሳተፍ ከተመደበ(ች)፣ተማሪው(ዋ) እና ወላጅ/አሳዳጊ በሚከተለው ሊንክ ላይ የሚገኘውን የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሥራ ልምምድ ፕሮግራም ስምምነት ማንበብ፣ መፈረም እና ማክበር አለባቸው፡- [ww2.montgomeryschoolsmd.org/departments/forms/pdf/280-77.pdf](ww2.montgomeryschoolsmd.org/departments/forms/pdf/280-77.pdf). ተማሪው(ዋ) ከጁን 22, 2026 እስከ ጁላይ 24, 2026 ባለው ጊዜ ውስጥ 75 ሰዓታትን ለማሟላት ተጨማሪ 25 ሰዓታትን ማጠናቀቅ ይጠበቅበ(ባ)ታል። ከሠመር ራይዝ "Summer RISE" መስፈርቶች በተጨማሪ፣ ወላጆች/አሳዳጊዎች የሚከተሉትን ማድረግ አለባቸው፡-
   a. ተማሪው(ዋ) በኢንተርንሺፕ ፕሮግራም ውስጥ እንዲሳተፍ/እንድትሳተፍ መስማማት እና የተማሪው(ዋ) በኢንተርንሺፕ ፕሮግራሙ ውስጥ በመሳተፍ ሊከሰት ለሚችል ማንኛውም ጉዳት የመጋለጥ አደጋን ግምት ውስጥ ማስገባት፤
   b. በአግባብ መገኘት እና የመከታተል መልካም የስራ ልምዶችን የማዳበር አስፈላጊነትን መተግበር፤
   c. ተማሪው(ዋ)ን ወደ ከኢንተርንሺፕ ድርጅት፣ ጣቢያ የሚያደርስ መጓጓዣ እንዳለው/እንዳላት ያረጋግጡ፤ እና
   d. ከፕሮግራም ጋር የተያያዙ ማናቸውም ስጋት ካሉዎት ከኢንተርንሺፕ አስተባባሪው ጋር ተገናኝተው ይነጋገሩ።
4. ሠመር ራይዝ ፕሮግራም/Summer RISE Program ላይ የሚሳተፉ ተማሪዎች በቅድሚያ በአካል ወይም ቨርቹወል ሙያዊ ክህሎት እና ስለ ፋይናንስ እውቀት አውደጥናት መሣተፍ እንዳለባቸው በመገንዘብ ተስማምቻለሁ። አውደ ጥናቱ የሚካሄደው ከሚፈለገው የፕሮግራም ሰአት በተጨማሪ መሆኑን በመገንዘብ ተስማምቻለሁ።
5 ሠመር ራይዝ ፕሮግራም/Summer RISE Program በአካል የሚሳተፉ ተሳታፊዎች ከያሉበት ቦታ የሙያ ልምምድ ወደሚያገኙበት ሥፍራ ለመመላለስ የመጓጓዣ አቅርቦት የራሳቸው ሃላፊነት መሆኑን ገብቶኝ ተስማምቻለሁ። "Youth Cruiser SmarTrip® Cards" በሁሉም የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ይገኛል።
6. በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የ Summer RISE ፕሮግራም ሠራተኞች ለተመዘገቡት ተማሪዎች በሙሉ ሙያዊ ትምህርት ልምምድ/Career Experience ለመስጠት የተቻላቸውን ጥረት ሁሉ ያደርጋሉ፣ የሆነ ሆኖ፣ Career Experiences የቦታ መገኘትን መሠረት በማድረግ የሚወሰን ይሆናል ይንንም በመገንዘብ ተስማምቻለሁ። የ "ሠመር ራይዝ ፕሮግራም" ሠራተኞች ተሳታፊ ተማሪዎችን በጅኦግራፊያዊ አመቺነት፣ በአካል እና/ወይም ቨርቹወል እንደአመቺነቱ እና ኢንዱስትሪ እንደተገኘ ሁኔታ ለማቀናጀት ይሞክራል።
7. የሠመር ራይዝ ፕሮግራም-ስንክልና ያላቸው ግለሰቦች የትምህርት ደምብ "Individuals with Disabilities Education Act (IDEA)" እና በተጓዳኝ የሜሪላንድ ህግ መስፈርት በሚፈለጉት ፕሮግራሞችና አገልግሎቶች ዉስጥ አለመካተቱን በመገንዘብ ተስማምተዋል።
8. የሠመር ራይዝ ፕሮግራም ተሳታፊዎች መርሃ ግብራቸውን በቀጥታ ከፕሮግራሙ መጀመር በፊት ከስራ ልምድ አስተናጋጅ ተወካይ(ዎች) ጋር የማስተባበር ሃላፊነት እንዳለባቸው ተረድተዋል እና ተስማምተዋል። የሙያ ልምድ ለመስጠት አስተናጋጁ ድርጅት ወይም ተወካዩ(ዎች) የሙያ ልምድ ተሳታፊው ከእነዚያ ሰዓታት ውጭ እንደሚጀምር/እንደምትጀምር ወይም እንደሚያጠናቅቅ/እንደምታጠናቅቅ ለሠመር ራይዝ ቢሮ በቅድሚያ ካላሳወቀ በስተቀር የሥራ ልምድ ሰዓቶች የሚተገበሩት ከሰኞ እስከ አርብ ከጠዋቱ 7፡00 AM እስከ ሠዓት በኋላ 6፡00 PM ባለው ጊዜ ውስጥ ብቻ ነው። የሙያ ልምድ ተቀባይ አስተናጋጆች ተወካይ(ዮች) ከቀኑ 9፡00 P.M. በላይ የተማሪ ተሳትፎን ሊጠይቁ አይችሉም።
9. የ "ሠመር ራይዝ" ተሳታፊዎች ጥሩ ክትትል የማድረግ ልምድ፣ ስነምግባር፣ ትክክለኛነት፣ ስነስርአት መጠበቅ፣ ሳይዘገይ ወዲያውኑ ማድረግ፣ ብስለት፣ ተገቢነት ያለው አለባበስ፣ አግባብ የሆነ የቢዝነስ ስነ-ምግባር፣ ማሳየት እንደሚጠበቅባቸው እና ቨርችወል የሚሳተፍ/የምትሳተፍ ከሆነ፣ እንደሚታወቀው በቪድኦ እንደሚሆን የሠመር ራይዝ ፕሮግራም "Summer RISE Program" ተሳታፊዎች "Career Experience Host Designee(s)" አማካይነት የማይፈታ ጉዳይ ካጋጠማቸው ለሠመር ራይዝ ፕሮግራም ቢሮ በኢሜይል [summer-rise@mcpsmd.org](mailto:summer-rise@mcpsmd.org) ወይም በስልክ ቁጥር 240-740-5599 ደውለው ማሳወቅ እንዳለባቸው በመገንዘብ ተስማምቻለሁ።
10. በሠመር ራይዝ ፕሮግራም ወቅት ለተማሪ ድጋፍ ለመስጠት እና ጥያቄዎች ሲኖሩ ለመፍታት የሠመር ራይዝ አስተማሪ አገናኝ መኮንን እንደሚመደብ በመገንዘብ ተስማምቻለሁ። አንድ ተማሪ በአካል በሚደረግ የስራ ልምምድ ለመሳተፍ ከመረጠ(ች)፣ የሠመር ራይዝ መምህር አገናኝ መኮንን ወይም የሰመር ራይዝ ሰራተኞች የተማሪው(ዋ)ን የሥራ ልምምድ በርቀት የመቆጣጠር አማራጭ ይኖራቸዋል ይህን በመገንዘብ ተስማምቻለሁ።
11. የስራ ልምምድ የሚሰጡ አካላት የማጣራት እና/ወይም ክትባቶችን የመሣሰሉ ተጨማሪ መስፈርቶች ሊኖራቸው እንደሚችል በመገንዘብ ተስማምቻለሁ። ጁን 22, 2026 የሠመር ራይዝ ፕሮግራም ከሚጀምርበት ቀን በፊት ማንኛውንም ተጨማሪ መስፈርቶችን ለማሟላት ከስራ ልምድ አስተናጋጅ/ተወካይ ጋር በቀጥታ መስራት የሰመር ራይዝ ፕሮግራም ተሳታፊዎች ሃላፊነት ነው። አንድ ተማሪ የአስተናጋጁን መስፈርቶች ማሟላት ካልቻለ(ች)፣ ከተገኘ ሌላ እድል ይጠብቃል/ትጠብቃለች ይህን በመገንዘብ ተስማምቻለሁ።
12. ተማሪው(ዋ) ሠመር ራይዝ ፕሮግራም ላይ በአካል በመገኘት ለመሳተፍ ከመረጠ(ች) እና ከኮቪድ-19 ጋር የተያያዙ ማናቸውም የተቀመጡ ገደቦች ካሉ፣ ተማሪው(ዋ) በራሱ(ሷ) ፈቃደኝነት እና በወላጆቹ/በአሳዳጊው ፈቃድ ይህንን እንደሚያደርግ/እንደምታደርግ በመረዳት ተስማምተዋል። በተቻለ መጠን፣ የሙያ ልምድ ተቀባይ አስተናጋጆች ተወካይ(ዮች) በሞንትጎመሪ ካውንቲ አስተዳደር እና በ MCPS የተቀመጡትን የኮቪድ-19 ፕሮቶኮሎች መከተል አለባቸው። ለኮቪድ-19 ለተጋለጠ(ች) ተማሪ MCPS ምንም አይነት ሃላፊነት እንደማይወስድ ግንዛቤ ተወስዷል።
13. የሠመር ራይዝ ፕሮግራም ተሳታፊዎች የገንዘብ ድጋፍ ክፍያ ለማግኘት ስለ ሠመር ራይዝ ፕሮግራም ልምዳቸው ቅድመ ዳሰሳ እና የፕሮግራም መጨረሻ ዳሰሳ ማጠናቀቅ እንዳለባቸው በመገንዘብ ተስማምተዋል።
14. የሙያ ዝንባሌ እና ችሎታን ከዝንባሌአቸው ጋር ለማመሣከር እንዲያመች የተማሪው(ዋ) መረጃ ለሙያ ልምድ ሰጪ/ተወካይ ይሰጣል። የሙያ ልምምድ ሰጪ/ተወካይ የሠመር ራይዝ ፕሮግራም ተሳታፊዎችን መረጃ የሚያገኙት እንደዝንባሌአቸው ለመመደብ እና/ወይም ከማን ጋር እንደሚቀናጁ ለማወቅ ስለሚረዳ ነው። ከሰመር ራይዝ ፕሮግራም ተሳታፊዎች የሚሰበሰቡ መረጃዎችን በሙሉ የሙያ ልምድ አስተናጋጅ እና ተወካዩ ለማናቸውም ለሶስተኛ ወገን እንደማያጋሩ በመገንዘብ ተስማምተዋል።
15. የሠመር ራይዝ ፕሮግራም ተሳታፊዎች ፕሮግራሙን በተሳካ ሁኔታ ካጠናቀቁ በኋላ ፈንድ ከተገኘ ለፕሮግራም ወጪያቸው እንደ ማካካሻ የሚቆጠር አበል እንደሚያገኙ ተስማምተዋል። MCPS የሠመር ራይዝ መርሃ ግብር ሲጠናቀቅ የተማሪው(ዋ)ን የስታይፐንድ ክፍያ ቼክ ለማዘጋጀት የተማሪው(ዋ)ን የመጀመሪያ እና የመጨረሻ ስም ቼኩን ለሚያዘጋጀው ባንክ ያስተላልፋል። የተማሪ አበል ክፍያ ቼክ በበቂ የገንዘብ ድጋፍ መገኘት ላይ የተመሰረተ መሆኑን ተረድቻለሁ፣ እና የሠመር ራይዝ ፕሮግራም ተሳታፊዎች ዝቅተኛውን 50-ሰአት መስፈርት ተሟልቶ ከተገኘ እና በሠመር ራይዝ ፕሮግራም ፅ/ቤት ከተረጋገጠ በኋላ በፕሮግራሙ ማጠቃለያ ላይ ቼካቸውን ይወስዳሉ። ቼክ ለመውሰድ በጋራ የሚመች ጊዜ አስቀድሞ ቀጠሮ ማስያዝ ያስፈልጋል። የሠመር ራይዝ ፕሮግራም ተሳታፊዎች ወይም ወላጆቻቸው/አሳዳጊዎቻቸው ስለ ተማሪ አበል ክፍያ ጥያቄ ካላቸው [summer-rise@mcpsmd.org](mailto:summer-rise@mcpsmd.org) ወይም 240-740-5599 በመደወል የሠመር ራይዝ ፕሮግራም ጽ/ቤትን "Summer RISE Program office" መጠየቅ ይችላሉ።ይህንን በመገንዘብ ተስማምተዋል።

16. የሠመር ራይዝ ፕሮግራም ተሳታፊዎች በሠመር ራይዝ ፕሮግራም መጨረሻ ላይ የስራ ልምድ ለመቅሰም በሠሩበት ተቋም የመቀጠር መብት እንደሌላቸው ለመቀጠር ምንም መጠበቅ እንደሌለባቸው በመገንዘብ ተስማምተዋል።

17. የሠመር ራይዝ ፕሮግራም ተሣታፊዎች የሰመር ራይዝ ፕሮግራም ሙያዊ ትምህርት ልምድ በሚወስዱበት ጊዜ የሙያ ልምድ አሰሪዎቻቸው ተቀጣሪዎች ሊሆኑ አይችሉም። የሙያ ልምድ ሰጪዎች ከሠመር ራይዝ ተሳታፊዎች የሥራ እንቅስቃሴ ምንም አይነት የራሳቸውን ጥቅም አይወስዱም፣ አንዳንድ ጊዜ እንደውም ሥራቸው ሊስተጓጎል ይችላል። የሰመር ራይዝ ፕሮግራም ተሳታፊዎች በቀጥታ በስራ ልምድ አስተናጋጆች ስራ ላይ እንደማይሳተፉ ወይም በመደበኛነት ወይም በተከታታይ (ፋይል ማዘጋጀት፣ ሌሎች የፅህፈት ስራዎች ወይም ደንበኞችን ማስተናገድ) እንደማይሰሩ በመገንዘብ ተስማምተዋል። የሙያ ሥራ ልምድ ሰጪዎች ለተማሪዎች ስለ ቢዝነሱ/ስለ ድርጅቱ እና በሥራ ድርሻቸው ላይ የሚያተኩሩ ኃላፊነቶች፣ እና ስለ ቢዝነሱ/የድርጅቱን የሥራ እንቅስቃሴዎች በሚመለከት ለተማሪዎች ሁሉ አቀፍ ግንዛቤ ይሰጧቸዋል። ተማሪው(ዋ)/ተማሪዎቹ እነዚህን ሥራዎች በመሥራት ጥራትን፣ ሙያን፣ እና ሥራ አስኪያጅ ወይም ማናጀር ውጤታማ ሆኖ የሚሠራበትን አሠራር እና በበርካታ የሥራ ቀጣሪ ድርጅቶች አካባቢ ለመጠቀም የሚያስችል ጠለቅ ያለ እውቀት ያገኛሉ ይህንን በመገንዘብ ተስማምተዋል።

18. የሠመር ራይዝ ፕሮግራም ተሳታፊ ይህን የስምምነት ውል፣ በሙያ ልምድ አስተናጋጆች የተሰጡትን ደንቦች እና መመሪያዎች፣ ወይም ሌላ ማንኛውንም ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የሠመር ራይዝ ፕሮግራም የተሰጡትን ደንቦች ካላከበረ(ች) MCPS በሚወስነው መሠረት፣የሠመር ራይዝ ፕሮግራም ሊቋረጥ የሚችል ሲሆን የአበል ድጎማውንም ለማግኘት ብቁ እንደማይሆን/እንደማትሆን በመገንዘብ ተስማምቻለሁ።

19. እርስዎ ወላጅ/ሞግዚት እንደመሆንዎ መጠን፥ ለተማሪ የሠመር ራይዝ የሥራ ልምድ ሰጪው ተቋም የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ድርጅት አለመሆኑን እንደነዚህ ያሉ ድርጅቶች የሙያ ልምድ አስተናጋጆች እንዲሆኑ የተመረጡት ለተማሪዎች በሚሰጡት የሙያ ልምድ ዕድል ጥራት ላይ በመመስረት ነው። የሙያ ልምድ ተቀባይ አስተናጋጆች ህጎችን፣ የትምህርት ቦርድ ፖሊሲዎችን እና የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ደንቦችን የመገምገም እና የማረጋገጥ ሃላፊነት አለባቸው። የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) እና/ወይም የሰመር ራይዝ ፕሮግራም ሰራተኞች የስራ ልምድ ተቀባይ አስተናጋጆችን እና/ወይም የስራ ልምድ አስተናጋጅ ተወካይ(ዮች)ን አይቆጣጠሩም ወይም አይከታተሉም ይህንን በመገንዘብ ተስማምተዋል።

20. እርስዎ ወላጅ/ሞግዚት እንደመሆንዎ መጠን ተማሪው(ዋ) በሠመር ራይዝ ፕሮግራም ከመሣተፉ(ፏ) ጋር በተገናኘ ምክንያት ምንም አይነት ተጠያቂነት ወይም ብልሽት ቢያጋጥም MCPS ተጠያቂ እንደማይሆን በመገንዘብ ተስማምተዋል።

## ተጨማሪ ስምምነት

ተማሪ ኦንላይን ሲመዘገብ- ወላጅ/ሞግዚት የሚከተሉትን የተስማሙ መሆናቸውን ተማሪው(ዋ) ማረጋገጫ ይሰጣል/ትሰጣለች፡-

1. ከተማሪ ጋር የሚደረጉ ግንኙነቶች—የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሠመር ራይዝ ፕሮግራም ሰራተኞች ወይም የስራ ልምድ የሚሰጠው ተቋም/ተወካዩ በሠመር ራይዝ ምዝገባ ቅጽ ላይ በተሰጠው MCPS ያልሆነ የተማሪ ኢሜል አድራሻ በመጠቀም ለተማሪ ኢሜል ማድረግ ይችላሉ። ያለፈቃድ/ያለስምምነት ከሶስተኛ ወገን ወደ MCPS የተማሪ ኢሜይል አካውንት ኢሜይሎችን ለመላክ ስለማይቻል ተማሪው(ዋ) መሳተፍ አይችልም/አትችልም። ከሙያ አስተናጋጅ/ተወካይ የሚመጡ የኢሜይል መልእክቶች የሚገናኙት ከሠመር ራይዝ ጉዳዮች ጋር ብቻ ነው። MCPS የሠመር ራይዝ ፕሮግራም ሰራተኞች ወይም የስራ ልምድ አስተናጋጅ ተወካይ ለተማሪው(ዋ) በሰመር ራይዝ የተማሪ መመዝገቢያ ቅጽ ላይ ከሠመር ራይዝ ፕሮግራም ጋር ተዛማጅ የሆኑ ጉዳዮችን ብቻ ከተማሪው(ዋ) በተሰጠው ስልክ ቁጥር በመጠቀም ሊደውሉለ(ላ)ት ወይም መልክት ለመላክ ይችላሉ።

   ❑ የተማሪዬ የሠመር ራይዝ ፕሮግራም ላይ የሚኖረው/የሚኖራት ተሳትፎ ሊሆንም ላይሆንም ስለሚችል የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ያልሆነ የኢሜል አድራሻን በመጠቀም የሰመር ራይዝ ፕሮግራም ሰራተኞች እና የስራ ልምድ ለመስጠት የሚያስተናግደው ድርጅት/ተወካይ የሠመር ራይዝ ፕሮግራም ጉዳዮችን ብቻ ግንኙነት ማድረግ እንደሚችሉ በመገንዘብ ተስማምተዋል።

2. የፎቶ እና የቪዲዮ መለቀቅ።

   ❑ የስራ ልምድ የሚሰጠው ተቋም/አስተናጋጅ በሠመር ራይዝ ፕሮግራም ወቅት ተማሪዬን ቪዲዮ ለመቅረጽ፣ ፎተግራፍ ለማንሳት፣ እና/ወይም ድምፅ ለመቅዳት በመፍቀድ ተስማምተዋል። እነዚህ ምስሎች እና/ወይም ቅጂዎች ያለ ምንም ተጨማሪ ማሳወቂያ ስለ ሠመር ራይዝ ለማስተዋወቅ ጥቅም ላይ ሊውሉ ይችላሉ። ለዚህ አጠቃቀም ለተማሪው(ዋ) ምንም ማካካሻ እንደማይደረግ እና ስለ ምስሎቹ፣ ቪዲዮዎቹ፣ እና ስለ ቅጂዎቹ ወይም በነዚህ የተቀናበረ ማንኛውም ስራዎች ሁሉ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) መብቶች የተጠበቁ መሆናቸውን በመረዳትና በመገንዘብ ተስማምተዋል።

   ❑ በሠመር ራይዝ ፕሮግራም ወቅት የስራ ልምድ የሚሰጠው/አስተናጋጅ ተቋም ተማሪዬን ቪዲዮ እንዲቀርፅ፣ ፎተግራፍ እንዲያነሳ እና/ወይም ድምፅ እንዲቀዳ አልፈቅድም/አልስማማም። <u>አለመስማማቴን/አለመፍቀዴን እስከ አርብ፣ ጁን 12, 2026 ለሠመር ራይዝ ቢሮ በዚህ የኢሜል አድራሻ summer-rise@mcpsmd.org ወይም 240-740-5599 በመደወል ማሳወቅ እንዳለብኝ ተረድቻለሁ። የፎቶ እና የቪዲዮ መልቀቅ ፈቃድ ላለመስጠት ምርጫዬ ቢሆንም ልጄ በሠመር ራይዝ ፕሮግራም ላይ መሳተፍ እንደሚችል/እንደምትችል ተረድቻለሁ።</u>

3. ነፃ ወይም ቅናሽ የተደረገባቸው ምግቦች (FARMS) መረጃ መስጠትን በሚመለከት—የሠመር ራይዝ ፕሮግራምን የሚያስተዳድረው MCPS በስራ ላይ የተመሠረተ ትምህርት ክፍል፣ ተማሪው(ዋ)ን ለመደገፍ እና ለጠቅላላ የሪፖርት አገልግሎት ዓላማ የተማሪው(ዋ)ን ነፃ ወይም ቅናሽ የተደረገባቸው ምግቦች (FARMS) አጠቃቀም ሁኔታ የሚገልፅ መረጃ ማግኘት ይፈልጋል። ይህ የተማሪ መረጃ ከ "MCPS Work-Based Learning office" በስተቀር ለውጭ ሰራተኞች ወይም ለሌላ አካል አይጋራም። <u>ማሳሰቢያ፡ ስለ FARMS መረጃ ከማጋራት መርጠው ቢወጡም ተማሪዎ በሠመር ራይዝ ፕሮግራም ላይ መሳተፍ ይችላል/ትችላለች።</u>

   ❑ MCPS የተማሪዬን FARMS መረጃ ለስራ-ተኮር ትምህርት ቢሮ እንዲያስተላልፍ በመፍቀድ ተስማምቻለሁ።

   ❑ MCPS የተማሪዬን FARMS መረጃ ለስራ-ተኮር ትምህርት ቢሮ እንዲሰጥ ፈቃደኛ አይደለሁም/አልስማማም።

4. መጓጓዣ—የሠመር ራይዝ ፕሮግራም የመጓጓዣ አገልግሎት አይሰጥም። በአካል የሚሳተፉ ተማሪዎች ወደ ሙያ ልምድ የሚያገኙበት ቦታ ለመጓጓዝ እና ለመድረስ የራሳቸው ሃላፊነት አለባቸው።

   ❑ የስራ ልምድ አስተናጋጅ ተቋም ወይም ተወካይ እና የሰመር ራኡዝ ሰራተኞች ተማሪዬን ከስራ ጋር ለተያያዙ ዝግጅቶች፣ በግል ወይም በስራ መኪና ተማሪዬን እንዲያጓጉዙ በመፍቀድ ተስማምቻለሁ። ለሚደርስ ማንኛውም አይነት ጉዳት MCPS ምንም አይነት ተጠያቂነት እንደማይኖርበት ተስማምቻለሁ።

   ❑ የስራ ልምድ የሚሰጠው አካል ወይም ተወካይ እና የሰመር ራይዝ ሰራተኞች ተማሪዬን እንዲያጓጉዙ አልፈቅድም/አልስማማም።

5. የባንክ መረጃ

   ❑ የሠመር ራይዝ ፕሮግራም የተማሪው(ዋ)ን የመጀመሪያ ስም እና የአያት ስም፣ የሠመር ራይዝ ፕሮግራሙን ሲያጠናቅቅ/ስታጠናቅቅ፣ የአበል ቼኩን ለመክፈል እንዲቻል አካውንቱን ለሚያስተዳድረው ባንክ እንዲያቀርብ ተስማምቻለሁ።

   ❑ የሠመር ራይዝ ፕሮግራም የተማሪዬን መለያ መረጃ የክፍያ ቼክ ለሚያስተዳድረው ባንክ እንዲያስተላልፍ አልፈቅድም/አልስማማም። ለተማሪዬ የሚሰጠው ድጎማ የተማሪዬን መጠሪያ ስም እና የአያት ስም ማግኘት በሚፈልገው ፈንዱን በሚያስተዳድረው ባንክ የሚወሰን መሆኑን ተረድቻለሁ። <u>ባለመፍቀዴ ምክንያት ተማሪዬ በፕሮግራሙ መጨረሻ ላይ የሚሰጠውን አበል እንደማያገኝ/እንደማታገኝ ተረድቻለሁ።</u>

## ፊርማ

በሠመር ራይዝ ፕሮግራም ለመሣተፍ የወላጅ/የሞግዚት ስምምነት መደረጉን ለማረጋገጥ የሠመር ራይዝ ፕሮግራም ተማሪ በኤሌክትሮኒክስ ይፈርማል/ትፈርማለች። በምዝገባ ወቅት፣ ጁን እና ጁላይ 2026 ድንገተኛ አደጋ ቢያጋጥም ለማግኘት እንዲቻል የወላጅ/አሳዳጊ ስም፣ ስልክ ቁጥር እና የኢሜይል አድራሻ ያስፈልጋል።